ቅጽ 1 | VOL 1

ታሕሳስ 2017 ዓም

# ሐሳብ አለኝ
## መጽሔት

ከተዳከመው የንባብ ባህላችን ጀርባ ያሉ እውነታዎች

ተፈጸመ!

ወጣት ዲፕሎማቶች ለምን የሉንም ?




# ድብቁ የወሲብ ገበያ

## ቴሌግራም ያቀጣጠለው የወሲብ አብዮት

## ዝግጅት

ኮንሰፕት ሀብ ኢትዮጵያ

ኢሜል:

concepthubethiopia@gmail.com

ማኅበራዊ ሚዲያዎቻችንን ለማግኘት

@concepthubeth

## ዋና አዘጋጅ

በረከት ጉዲሳ

አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ

0913134524

## የዚህ ዕትም አምዳኞች

ምንተስኖት ደስታ

አልታዬ ኪዳኔ

ዙፋን ክፍሌ

ሌንሳ እንዳለ

ደምሰው ሺፈራው

## የመጽሔት ዲዛይን

ሰሎሞን ሸዋረጋ

## ዲጂታል ህትመት ሥርጭት

ቲክቫህ ማጋዚን የቴሌግራም ገጽ

@tikvahethmagazine

# መልእክት

ውድ አንባቢያን ይህ <<ሐሳብ አለኝ>> የተሰኘው የመጀመሪያ ዕትም ዲጂታል መጽሔት በአቀራረቡም ሆነ በአዘገጃጀቱ ለየት ያለ ሐሳብ ይዞ ብቅ ያለ ነው፡፡ የዚህ መጽሔት ዝግጅት በውስጡ ሦስት መሰረታዊ ዓላማዎችን የያዘ ነው፡፡ የመጀመሪያው ጥሩ ሙያዊ ክህሎትና እውቀት እንዲሁም የመጽሐፍና የማንበብ ልምድ ያላቸው ብዙ ወጣቶች ያሉ ቢሆንም ሐሳባቸውን የሚያካፍሉበት፤ የሚወያዩበት እና የሚሟገቱበት የወጣቶች መድረክ አነስተኛ በመሆኑ፥ አቅም ያላቸውን ወጣቶች ለማስተዋወቅ በማሰብ የተጀመረ ነው፡፡ ሁለተኛው ደግሞ በሀገራችን አብዛኛው የህብረተሰብ ክፍል ወጣት እንደመሆኑ መጠን በብዙ ሀገራዊ ጉዳዮች ላይ አቋሙን የሚያንጸባርቅበት፤ ግብዓት የሚሰጥበት፤ ድምጹን የሚያሰማበት፤ ሞያዊ ትችቶችን የሚያቀርብበት፤ የሚማማርበት፤ የንባብ ባህሉን እና የውይይት ክህሎቱን የሚያዳብርበት ነጻ መድረክ ለመፍጠር በማቀድ የተዘጋጀ ነው፡፡ ሦስተኛው ወጣቱ ሐሳቡን በሰለጠነ እና በሳል በሆነ መንገድ ከመግለጽ ባለፈ የመጽሔቱ አምደኞች ክፍያ እንዲያገኙ ማስቻልና መጥቀምን፤ ከተለያዩ ተቋማት ጋር በተለይም በማኅበራዊ ጉዳዮች ላይ አብሮ በመስራት ወጣቱ ዘንድ ያለውን እምቅ አቅም ማሳየት እና የሥራ ትስስሮችን መፍጠርን ግቦቹ አድርጎ ተነስቷል፡፡

በመሆኑም ይህ መጽሔት በአዘገጃጀቱ ለየት ያለ ነው ስንል፥ በዚህ መጽሔት የሚሳተፉ ጸሐፊዎች በሙሉ በሚባል መልኩ ቋሚ አምደኞች ሳይሆኑ ጹሑፋቸውን ለማሳተም የጠየቁ ወጣቶች ናቸው፤ ወደፊትም <<ሐሳብ አለኝ መጽሐፍ ፈልጋለሁ>> የሚል ወጣት በሙሉ ጹሑፉን በተጠቀሱት አድራሻዎች በመላክ መሳተፍ ይችላል፡፡ በአቀራረቡም ለየት ያለ ነው ስንል ወቅትን ጠብቆ የሚወጣ መጽሔት አይደለም፡፡ ከላይ እንዳነሳነው ይህ መድረክ ለወጣቶች የተዘጋጀ አማራጭ መድረክ እንደመሆኑ እንደ እንደሚኖረው ተሳትፎ መጠን የመጽሔት ዝግጅቱም እየጨመረ የሚሄድ ይሆናል፡፡ መጽሔቱን ከማውጣት በተጨማሪም በቀረቡ ጹሑፎች ላይ ውይይቶችን በማዘጋጀት ሐሳቦች እንዲንሸራሸሩ ያደርጋል፡፡

ይህ ከሆነ <<ወጣቱን በቀላሉ የሚስቡ በርካታ መንገዶችና አማራጮች እያሉ ለምን የንባብ ልምዱ አነስተኛ በሆነበት ጊዜ በመጽሔት መልክ መምጣት አስፈለገ?>> የሚል ጥያቄ ሊነሳ ይችላል፡፡ እንደተባለውም በዚህ ወቅት የንባብ ልምዱ በተለያዩ መክንያቶች እየተቀዛቀዘ ቢሆንም ትውልድ በዚህ የማንበብ እና የመጽሐፍ ልምምድ ውስጥ ማለፉ ግዴታ ነው፡፡ ለዚህም ይበልጥ የሚያዳክም ሳይሆን የሚያቀራርብ፤ እየዘመነ የሚሄድ እና የሚያነቃቃ አማራጮች ያስፈልጉታል፡፡ በዚህ መጽሔት ወጣቶች በሙያቸውና በክህሎታቸው በየአከባቢያቸው ጥናቶች እንዲያደርጉ፤ ለችግሮች የመፍትሔ ሐሳብ እንዲያቀርቡ እና ተወዳዳሪ እንዲሆኑ ዕድል ይመቻቻል፡፡ ለዚህ ደግሞ የማንበብ አከባቢን የማስተዋልና የመጠየቅ ክህሎትን ማዳበር ሲያስፈልግ በዚህ መልኩ የተጠና የተደራጀ ሐሳብን ለማቅረብ ደግሞ መነሻው ጹሑፍ ነው፡፡ ከላይ እንደተጠቀሰው በጹሑፍ የቀረቡ ሐሳቦች ግን በተለያዩ አማራጮች የማቅረብ ሥራ ይሰራል፡፡

በመጨረሻም ይህ የወጣቶች መድረክ በሀገር አቀፍ ደረጃ እንዲሁም በዓለም አቀፍ ደረጃ በሞያቸው፤ በክህሎታቸው እና በእውቀታቸው ለሰብዓዊ መብት ክብር የሚቆሙ፤ ለማኅበረሰባዊ ንቃት የሚታገሉ፤ ስለህጻናትና ሴቶች ጥቃት ግድ የሚላቸው፤ የጥላቻ ንግግርና ሐሰተኛ መረጃን የሚፋለሙ፤ የአየር ንብረት ለውጥ የሚያሳስባቸው፤ ስለሰላም ዘብ የሚቆሙ፤ ስለትምህርት ጥራት የሚቆረቆሩ፤ ስለወጣቱ የሚሟገቱ፤ እና መሰል ንቁ ወጣቶችን እንደሚያሳየን እምነታችን ነው፤ ለዚህም ወጣቱ እንዲሳተፍ ጥሪ እናቀርባለን፡፡

በዚህ መጽሔት የቀረቡት ጹሁፎች ይዘት እና ትክክለኛነት ለማረጋገጥ የምንችለውን ጥንቃቄ እናደርጋለን፡፡ በዚህ የዲጂታል መጽሔት ውስጥ የተካተቱ ጹሑፎች ሙሉ ለሙሉ የጸሐፊውን አቋምና ሀሳብ እንጂ የአሳታሚውን አቋም አይገልጹም፡፡ በዚህ መጽሔት የተካተቱ የጹሑፍ ዝግጅቶችን መልሶ በማሳተም፤ በድምጽና በቪዲዮ እንደገና ለመጠቀም፤ ለማባዛትም ሆነ ለማሰራጨት የአሳታሚው የጹሁፍ ፍቃድ ያስፈልጋል፡፡

© 2017 ኮንሰፕት ሀብ ኢትዮጵያ

# ይዘት
# Content




5
ድብቁ የወሲብ ገበያ፡ ቴሌግራም ያቀጣጠለው የወሲብ አብዮት



9
ከተዳከመው የንባብ ባህላችን ጀርባ ያሉ እውነታዎች




17
ተፈጸመ! ፡ ግጥም



18
ወጣት ዲፕሎማቶች ለምን የሉንም ?

# ይህ ቦታ
# ለማስታወቂያ
# ክፍት ነው!



# ድብቁ የወሲብ ገበያ፡ ቴሌግራም ያቀጣጠለው የወሲብ አብዮት




በምንተስኖት ደስታ

በፈረንጆቹ 2013 አማራጭ የመልዕክት መለዋወጫ ሆኖ የኢንተርኔቱን አለም የተቀላቀለው ቴሌግራም ወደ 1 ቢሊዮን የሚጠጉ ተጠቃሚዎችን ማፍራት ችሏል። መተግበሪያው ቀላል፣ ምቹና ደህንነቱ የተጠበቀ መሆኑና በአንድ ቡድን ውስጥ በርካታ አባላትን መያዝ መቻሉ በብዙዎች ዘንድ ምቹ ተመራጭ እንዲሆን አድርጎታል። መተግበሪያ በሜታ ኩባንያ መተግበሪያዎች ላይ በተነሱ የደህንነት ሥጋቶች፣ በዶናልድ ትራምፕ የማህበራዊ ሚዲያ ዕግድ፣ በዩክሬን ራሺያ እንዲሁም በመካከለኛው ምሥራቅ ጦርነቶች ምክንያት ከፍተኛ ተጠቃሚዎችን ችሏል።

ወደ ሀገራችን ስንመጣ ሀገራችን ኢትዮጵያ ሰፊ የቴሌግራም ተጠቃሚዎች ያሏት ሀገር ስትሆን በሲሚላር ዌብ ጥናት[1] መሠረት ቴሌግራም የኢትዮጵያውያን ቁጥር አንድ የመልዕክት መለዋወጫ እንደሆነ ይጠቀሳል። በዝቅተኛ የኢንተርኔት አቅም መስራት መቻሉ፣ የንግድና የፖለቲካ እንቅስቃሴዎችን ለማድረግ ምቹ መሆኑ ቴሌግራም በኢትዮጵያ ተመራጭ እንዲሆን አስችሎታል። የኮሮና ወረርሽኝ የወለደው ኢንተርኔትን መሠረት ያደረገው አዲስ የትምህርትና የሥራ ባህል በኢትዮጵያ የቴሌግራም ተጠቃሚዎችን ቁጥር ከፍ አድርጎታል።[2] በመሆኑም የሀገሪቱን ጠቅላይ ሚንስትር ጨምሮ የመንግስት ተቋማት፣ የግል ድርጅቶች፣ ተፅዕኖ ፈጣሪ ግለሰቦች ከማህበረሰቡ ጋር ለመገናኘት ተመራጭ መንገዳቸው አድርገውታል። ቴሌግራም ጀማሪ ሥራ ፈጣሪዎችን ከደንበኞች ጋር ለማገናኘት፣ ለትምህርትና ለመረጃ ልውውጥ አወንታዊ ሚናን ቢጫወትም ላልተረጋገጡ መረጃዎችና የሤራ ትንተና፣ ማንነትን መሠረት ላደረጉ ጥቃቶች፣ ለህገወጥ ንግዶች፣ ለገንዘብ ማጭበርበርና ለመሳሰሉት ተጠቃሚዎችን ማጋለጡን የተለያዩ ሪፖርቶች ይጠቁማሉ። በዚህ ፅሁፍም ቴሌግራም ከሚታማባቸው ጉዳዮች አንዱ የሆነውን ልቅ የወሲብ ገበያ ከኢትዮጵያ አንፃር እንዳንስስ።


ስሙ ዳንኤል[3] ይባላል የድሬደዋ ነዋሪና የዩንቨርስቲ ተማሪ ነው በቴሌግራም ለሚፈፀሙ የሳይበር ወሲብ[4] ተግባራት እስከ ስድስት ሺህ ብር በወራት ውስጥ እንዳወጣ ይናገራል። ዳንኤል ከወራት በፊት እንደ ቀልድ ቴሌግራም ላይ ያገኘው የሳይበር ወሲብ አገልግሎት ሱስ እንደሆነበትና ለመውጣት እንዳዳገተው ይገልፃል።

እንደ ዳንኤል ያሉ ወጣቶችን ሰለባ ያደረገው' የሳይበር ሴክስ አብዮት በሀገራችን ከተጀመረ ከአምስት አመት በላይ እንደሆነው ለዚሁ አላማ የተከፈቱ የአንዳንድ ቻናሎችና ግሩፖች እድሜ ይናገራል። ነገር ግን ከፍተኛ መስፋፋትን

1 https://www.similarweb.com/blog/research/market-research/worldwide-messaging-apps/
2 https://www.lolinemag.com/articles/why-telegram-became-the-go-to-platform-in-ethiopia/

3 ለደህንነቱ ሲባል ስሙ የተቀየረ
4 ሳይበር ሴክስ በኢንተርኔቱ አለም ለሚካሄዱና አካላዊ ላልሆኑ ግንኙቶች የተሰጠ ስያሜ ሲሆን በውስጡ የሳይበር የወሲብ ንግድ (Cyber prostitution)፣ ሴክስቲንግ፣ ፎንሴክስ፣ ሊቭ ሴክስና cyber pornን የሚያጠቃልል ቃል ነው። https://www.smsna.org/patients/did-you-know/what-is-cybersex

ያሳየው ከኮሮና ቫይረስ በቤት መቆየት በኋላ መሆኑን ለዚህ ጽሑፍ ዝግጅት ዳሰሳ የተደረገባቸው የቴሌግራም ግሩፖችና ቻናሎች እንቅስቃሴ ያሳያል፡፡ በተለይም የሐገሪቱ ከፍተኛ የኢንተርኔት አቅራቢ የሆነው ኢትዮቴሌኮም ከአንድ አመት በፊት የፖርን ገጾች እንዲወርዱ[5] ካደረገ በኋላ በቴሌግራም ፖርንን መመልከትና ተያያዥ ተግባራት መስፋፋታቸውን መመልከት ተችሏል፡፡




ግሩፖችና ቻናሎቹ ስሞቻቸውንና የዘርኤማቸውን ለመሠየም ወሲብ ነክ በሆኑ ቁልፍ ቃላት ሲጠቀሙ በአማካይ ከ500 እስከ 10ሺ አባላት/ተከታዮች አሏቸው በውስጣቸውም ልክ እንደ ሲንጋፖር አቻዎቻቸው[6] አባላቶቻቸውን ከተቃራኒም ሆነ ከተመሳሳይ ጾታ ጋር ለአልጋ ማገናኘት፣ የቪዲዮ፣ የድምፅ፣ የቻት የወሲብ አገልግሎት ማቅረብ፣ የወሲብ ቪዲዮዎችን መሸጥ፣ ከባህል ተቃራኒና ፀያፍ የወሲብ ልምምዶችን በታሪክና በቪዲዮ ማለማመድ፣ ወሲብ ነክ የሆኑ መድሃኒቶችና ቁሳቁሶችን የመሸጥ ሥራ ይሠራሉ፡፡

የዚህ ፅሁፍ አዘጋጅ በተወሰኑ ግሩፕ ላይ ካሉ ምልልሶችና ውይይቶች እንደተረዳው ለዲጂታል ወሲብ አገልግሎቶች ከ500 - 3000 ብር ይጠየቃል፡፡

በዚህ የወሲብ ንግድ የተሰማሩ አካውንቶች በየጊዜው ፕሮፋይላቸውን የሚቀያይሩ ሲሆን በገጻቸው ላይ የሚገኘው ስማቸውና ክፍያ ለመፈጸም የሚጠቀሙባቸው የቴሌ ብርና የባንክ አካውንት ስያሜዎች የተለያዩና አንዳንዴም የተቃራኒ ጾታ ሲሆን እንዲህ በሚሆንበት ወቅት አካውንቱ የፍቅረኛዬ ነው፣ የወንድሜ ነው፣ የኔ እንቢ ስለሚል ነው፣ ሲሙን ያወጣሁት በሌላ ሰው ነው አይነት መሰል ምክንያቶችን ይደረድራሉ በአንጻሩ የቴሌግራም ቦትን በመጠቀም ማንነታቸውን ሙሉ ለሙሉ ደብቀው የሚንቀሳቀሱም አሉ፡፡ ብዙሃኑ የ”ሴቶች” ተብለው በተከፈቱ አካውንቶች በአብዛኛው የሚያወሩት ወንዶች መሆናቸውና ቅድሚያ አስከፍለው ብር ከተቀበሉ በኋላ ከፋዩን ብሎክ እንደሚያደርጉና አንዳንዶችም ሀሰተኛ ቪዲዮዎችን እንደሚልኩ ከምልልሱ ለመረዳት ችሏል፡፡




የወሲብ ቪዲዮዎችን በተመለከተ “የሀገር ውስጥ” እና “የህፃናት” የሚባሉ የወሲብ ቪዲዮዎች ከፍተኛ ክፍያ የሚጠየቅባቸው ሲሆኑ ከባህል ያፈነገጡ እንዲሁም በሃይል የሚፈፀም ወሲብ (አስገድዶ መድፈርን) የሚያሳዩ ቪዲዮዎችም እንዳሉ ለመታዘብ ተችሏል፡፡ የሀገርኛ የወሲብ ክምችቶች የሚሰበስቡት ለማስታወሻ በሚል ከፍቅረኞቻቸው ጋር የሚደረጉ አካላዊም ሆነ የኦንላይን የወሲብ ግንኙነታቸውን ከሚቀዱ ጥንዶች፣ በመፀዳጃ ቤት፣ በፔንስዮንና በመታጠቢያ ቤት ከተገጠሙ ድብቅ ካሜራዎች፣ በግድ ከሚደረጉ የቪዲዮ ቀረፃዎችና ከአንዳንድ 18+ የቪዲዮ ስትሪሚንጎች ሲሆን በቪዲዮዎቻቸው መለጠፍ ምክንያት ለበርካታ ችግሮች የተጋለጡና ራሳቸውን ያጠፉ ሴቶችም እንዳሉ መስማት የተለመደ ነው፡፡ አንድ በዚህ ሽያጭ የተሰማራ አካውንት ጋር በተደረገ ልውውጥ ቪዲዮው የአርቲስቶችና የታዋቂ ሰዎች ሲሆን ዋጋው እንደሚጨምር ተመልክቷል፡፡

5 https://www.linkedin.com/posts/birukfekadu_porn-activity-7113625220761952256-vvYV/

6 https://www.straitstimes.com/singapore/telegram-channels-offer-explicit-sex-videos-photos-for-a-fee-in-similar-vein-to-sg-nasi-lemak

ሌላው እጅግ የሚያስደነግጠውና ብዙ ፈላጊ እንዳለው ለመታዘብ የተቻለው የህፃናት ወሲብ ነው። በነዚህ የወሲብ ቪዲዮዎች ላይ እድሜ ያቸው 15 እንኳን የማይሟላቸው ህፃናት ከአዋቂዎች ጋር ወሲብ ሲፈፅሙ የሚታዩ ሲሆን እንደዚህ አይነት ቪዲዮዎች ተፈላጊ መሆናቸው አሁን ላይ እየተባባሰ የመጣው የህፃናት የወሲብ ጥቃት ነገም ላይ ከአሁን በከፋ ላለመፈጠሩ መተማመን እንደማንችል ያስረዳናል።

ከዚህ ጋር ተያይዞ መድፈርን የሚያበረታቱና የተደፈሩበትን ቀን እንደ ደስታ የቆጠሩ ባለታሪኮች እንደፃፏቸው ተደርገው የሚቀርቡና አንዳንዴም በሴቶች የሚተረኩ ወሲባዊ ታሪኮች ህፃናትን፣ የቤት ሰራተኞች፣ ዘመዶችና ተከራዮችን ትኩረት ያደረጉ ጥቃቶችንና ወሲባዊ ግፊቶችን የሚያበረታቱ ናቸው። ከባህል ተቃራኒ የሆኑ የግብረ ሰዶም ልምድን ከማበረታታት ባሻገር የማገናኘት ሥራም ይሠራሉ

እነዚህ ገፆች ህገወጥ እና ከህክምና ምክር ውጭ የሆኑ የመድሀኒትና የወሲብ ቁሳቁስ ሽያጭና ያልተረጋገጡ የሥነፈተ ወሲብና መሰል አገልግሎቶችን እንደሚሰጡ የሚያስነግሩ ሲሆን መድሐኒቱም ሆነ ዕቃዎቹ ተገቢውን ህጋዊና ሞያዊን ፍተሻ ጠብቀው የማይገቡና አንዳንዶቹም በህጋዊ መንገድ ወደ ሀገር የሚገቡ ሲሆን መድሐኒቶቹ ያለ ሐኪም ዕርዳታና ያለበቂ ማማከር ከተወሰዱ አደጋ ላይ የሚጥሉ ናቸው።

በባህል ህክምና ስም ለሚፈጸሙ ጉዳቶች ተጋላጭ ዕንደሚያደርግ ማህበሩ ቢያሳስብም[7] የባህል ህክምና እንደሚሰጡ የሚያስነግሩት ግለሰቦችም በኢትዮጵያ የባህል ህክምና አዋቂዎች ማህበር ያልተመዘገቡና በህጋዊ ማዕቀፍ ሥር ያልታቀፉ መሆናቸውን በማስታወቂያው ላይ በተጠቀሱ ስልኮች ከተደረገ ልውውጥ ማረጋገጥ ተችሏል።

የቴሌግራምን የደህንነት ፖሊሲ ሽፋን በማድረግ የሚፈጸሙ እንደዚህ አይነት እንቅስቃሴዎች ወጣቶች የፖርኖግራፊ፣ ሴክስተንግ[8] ሱስ ተጋላጭና ጥንቃቄ ለጎደለው ወሲባዊ ልምምዶች ከማድረጉ[9] ባሻገር ለህጻናትና ለጾታዊ ጥቃቶች መሸፋፋት፣ ለግለሰባዊ የነጻነት መብት ጥሰት፣ ራስን ለማጥፋትና ላጎንዮሽ የጤና ጉዳቶችና ለህገ ወጥ የንግድ እንቅስቃሴ መስፋፋት የሚኖራቸው አስተዋጽዖ ከፍተኛ ቢሆንም በቴሌግራም ድርጅትም ሆነ በሚመለከታቸው መንግስታዊና መንግስታዊ ያልሆኑ ክፍሎች ትኩረት እንደተነፈገው ያሳያል።

የቴሌግራም ተቋም የፖርኖግራፍ ቪዲዎችንና ወንጀሎችን ለሚለቁ ግሩች፣ ቦቶችና ቻናሎች ሪፖርት የሚደረግበት ሥርዓት ቢፈጥርም ሪፖርቱን መሰረት አድርጎ እርምጃ ሲወስድ አይታይም። ምናልባት ተወሰደ የሚባለው እርምጃ የማስጠንቀቂያ ምልክት በገጹ ላይ መለጠፍና ከአይኦስ (አይፎንና የአፕል ፕሮዳክቶች) ላይ ማንሳት ነው። ነገር ግን የቴሌግራም ፋይሎች በቀላሉ የሚጋሩና ከጠፉ በኋላ ጭምር በክላውድ የማይደመሰሱ[10] በመሆናቸው ከዚህ የከፋ ዕርምጃ መውሰድ ይኖርበታል።

ይህንን ተግባራዊ ዕንዲያደርግና ቴሌግራም የሀገሪቱን ህግና የተጠቃሚዎችን ደህንነት እንዲጠበቅ የማድረግ ሃላፊነቱን እንዲወጣ የአውሮፓ ህብረትና ብራዚል እንዳደረጉት[11] ሁሉ የሚመለከታቸው የመንግስት አካላት ተቋሙ ላይ ጫና ሊያሳድሩ ይገባል። ከዘህ ባሻገር ቤተሰብ የልጆቻቸውን የስልክና የማህበራዊ ሚዲያ አጠቃቀም ሊቆጣጠሩና ግለሰቦች ግላዊነታቸውንና ደህንነታቸውን ሊጠብቁ ይገባል።

7 https://www.ethiopianreporter.com/53642/

8 ወሲባዊ መልዕክቶችን የመላላክ

9 Sexting and high sexual risk-taking behaviours among school youth in northern Ethiopia: estimating using prevalence ratio: https://sci-hub.se/10.1136/bmjsrh-2018-200085

10 https://dl.acm.org/doi/fullHtml/10.1145/3677117.3685008#:~:-text=Unfortunately%2C%20Telegram%20has%20become%20famous,channels%20%5B24%2C%2035%5D

11 https://t.me/durov/346 (ከቴሌግራም መስራች ይፋዊ የቴሌግራም ገጽ የተወሰደ)

## ስለ አዘጋጁ


የዚህ ጽሑፍ አዘጋጅ በሥነ ሕብረተሰብ (ሶሲዮሎጂ) ከሐረማያ ዩንቨርስቲ የተመረቀ ሲሆን በአሁን ሰዓት በስንቅ ዩዝ ኢኒሼቲቭ በፕሮጀክት ኮርዲኔተርነት እየሰራ ይገኛል። አዘጋጁ ከዚህ ቀደም በሐረማያ ዩንቨርስቲ የሶሲሎጂ ዲፓርትመንት በረዳት መምህርነት ያገለገለ ሲሆን እንዲሁም በሕብረተሰብ ጤና ኢንስቲቲዩት ለሳውዲ ተመላሽ ወገኖች በተቋቋመው የአእምሮ ጤናና ሠማህበራዊና ሥነ ልቦናዊ ድጋፍ ቡድን /EPHI - MHPSS team/ ውስጥ ሰርቷል።

+251 967 537 965 menetasnot1@gmail.com




# ይሳተፉ ገቢ ያግኙ!

@concepthubeth

## ቴሌግራም ቻናላችን ቤተሰብ በመሆን ይሳተፉ!

# ከተዳከመው የንባብ ባህላችን ጀርባ ያሉ እውነታዎች

አልታየህ ኪዳኔ

## መንደርደሪያ

ደራሲ ሌሊሳ ግርማ ለ 20 አመታት ገደማ በስነ ጽሑፍ አለም ቆይቷል፡፡ በቅርቡ ደማቆቹ የተሰኘ አዲስ የልቦለድ ትርጉም ስራ ያሳተመ ሲሆን 8 መጻሕፍትንም ለአንባቢያን አድርሷል፡፡ ደራሲው በአሁኑ ወቅት ለሕትመት ዝግጁ የሆኑ ስራዎች አሉት፡፡ እዚህን ስራዎች ለገበያ ካበቃ በኋላ፤ ሌሎች አዳዲስ ሥነ-ጽሑፋዊ ስራዎቹን ለህትመት እንደማያዘጋጅ ተናግሯል፡፡

የሙሉ ጊዜ ደራሲ የሆነው ሌሊሳ አሁን ባለው ሁኔታ መጽሐፍ እየጻፉ ማሳተም አስቸጋሪ እንደሆነ ይገልጻል፡፡ የስነጽሑፍ ስራን ማሳተም፤ ማከፋፈል፤ የወጣበትን ወጪ ማስመለስ ከጊዜ ወደጊዜ አዳጋች እየሆነ መምጣቱን የገለጸው ደራሲው ጽሁፍ መጻፉን ባያቆምም “ስነጽሁፍን እንደ መደበኛ ስራ መስራት” ሊያቆም መሆኑን አስረድቷል፡፡

> “ሃያ ዓመት የለፋነው ለምንድነው? ብዬ ራሴን እጠይቀዋለሁኝ..... ሥነ ጽሑፍ ከሁሉ የሚያለፋው፣ ከሁሉ የሚያስጨንቀው፣ ከሁሉ ትውልድ የሚያንጸው ሆኖ ሳለ ለምን ከሁሉ የተጨቆነ ሆነ? መቼ ነው ከማስታወቂያ ያለፈ መጽሐፍን ለማስነበብ የጀርባ አጥንት ያለው ሥራ የሚሠራው?



photo source: Facebook (Yetebarek Walelegen)

ሌሊሳ በቅርቡ ከሕትመት ዋጋ መናር ጋር በተያያዘ የደራሲያን ልፋት እና ውጤት አለመጣጣም እንዳሳሰበው ገልጾ ነበር፡፡(1) የሥነ ጽሑፍ ብሎም የደራሲዎች መፃኢ እጣ ፈንታ እንደሚያሳስበው በዚሁ ጊዜ የገለጸው ደራሲው "ሥነ ጽሑፍ የተናቀ ነገር መሆኑ ያሳስበኛል፤ ይቆጨኛል'' ብሏል፡፡

ሥነ ጽሑፍ እንደ ሌሎቹ የጥበብ ዘርፎች መጠነኛ ክብር፣ አገልግሎት እና ዋጋ ለምን እንዳላገኘ የሚጠይቀው ሌሊሳ "…ሃያ ዓመት የለፋነው ለምንድነው? ብዬ ራሴን እጠይቀዋለሁኝ…ሥነ ጽሑፍ ከሁሉ የሚያለፋው፣ ከሁሉ የሚያስጨንቀው፣ ከሁሉ ትውልድ የሚያንጸው ሆኖ ሳለ ለምን ከሁሉ የተጨቆነ ሆነ? መቼ ነው ከማስታወቂያ ያለፈ መጽሐፍን ለማስነበብ የጀርባ አጥንት ያለው ሥራ የሚሠራው?…" በማለት ቁጭቱን ገልጿል፡፡፡

## በቅርብ ጊዜአት ፈተና የተደራረበበት የመጻሕፍት ህትመት ዘርፍ

በ2016 ዓ.ም ለመጻሕፍት ህትመት ዘርፍ "ከባድ ዓመት" እንደነበር በመጻሕፍት ንግድና ህትመት ላይ የተሰማሩ ሰዎች ይናገራሉ፡፡ የሕትመት ግብአቶች ዋጋ መናር፤ የማክሮ ኢኮኖሚ ማሻሻያው እና በቅርቡ መጻሕፍት ላይ የተጣለው የተጨማሪ እሴት ታክስ ተደራራቢ ፈተናዎችን ይዞ እንደመጣም ይገልጻሉ፡፡

ከውጭ የሚገቡ የወረቀት፣ ቀለም፣ ኮላ እና ተያያዥ የህትመት ግብዓቶች ዋጋ በሸቀጦች የዋጋ ንረት እና በዶላር ጭማሪው ምክንያት እንደናሩ ከ30 ዓመታት በህትመት እና ሽያጭ ላይ የቆዩት አቶ ዓይናለም መዋ ተናግረዋል፡፡ በ2 ኪሎ ተኩል ቀለም ላይ ከ400 እስከ 500 ብር ጭማሪ መታየቱንም የሚጠቅሱት አይናለም ከዶላር ጭማሪው በፊት 3ሺ ብር የነበረው አንድ ሪም (እሽግ) ወረቀት 4ሺ ብር እንደገባ ይናገራሉ፡፡ ይህንን ተከትሎም የመጻሕፍት ዋጋ አልቀመስ ብሏል፡፡

ወረቀት ለመጻሕፍት ህትመት ዋነኛ ግብአት ነው፡፡ ለመጻሕፍት ህትመት የሚያገለግሉት ወረቀቶችም የሚገቡት ከውጭ አገራት ነው፡፡ ደረጃውን የጠበቀ የህትመት ወረቀት በሀገር ውስጥ ሊመረት አለመቻሉ ለዘርፉ ፈተና ሆኗል፡፡ ባለሀብቶች በሀገር ውስጥ በወረቀት ማምረት ስራ ላይ አለመሰማራታቸው ለወረቀት መወደድ በምክንያትነት እንደሚጠቀስ የደራሲያን ማህበር ፕሬዝዳንት አበረ አዳሙ ይገልጻሉ፡፡

የወረቀት አስመጪዎች በጣም ጥቂት መሆናቸው ለዘርፉ ሌላ ፈተና መሆኑን የሚናገሩት አቶ አበረ፤ ማህበሩ ከአመታት በፊት በሰራው ጥናትም ህጋዊ የወረቀት አስመጪዎች ቁጥር 2 ብቻ እንደነበሩ ያስታውሳሉ፡፡

የመጻሕፍት ሕትመት በወረቀት እና ሌሎች ግብአቶች መወደድ እየተፈተነ ባለበት በዚህ ወቅት፤ በሰኔ 27/ 2016 ዓ.ም. ጸድቆ በስራ ላይ የዋለው አዲሱ የተጨማሪ እሴት ታክስ አዋጅ መጻሕፍትን የተጨማሪ እሴት ታክስ ውስጥ አካትቷል፡፡ አዋጁ ከቅዱሳን መጻህፍት ውጪ ሌሎች መጻሕፍት የተጨማሪ እሴት ታክስ ውስጥ እንዲካተቱ ይደነግጋል፡፡

አዋጁ ዘርፉን "በደንባራ በቅሎ ቃጭል ተጨምሮ እንዲሆን አድርጎታል" ያሉት አቶ አይናለም ከተጨማሪ እሴት ታክስ አዋጁ በኋላ የመጻሕፍ ዋጋ ከ20 እስከ 30 በመቶ እንደጨመረ ግምታቸውን ያስቀምጣሉ፡፡

ጠበቃ እና የህግ አማካሪ የሆኑት አቶ ወንድሙ ኢብሳ በበኩላቸው መጻሕፍት ላይ የተጨማሪ እሴት ታክስ መጣሉን ይተቻሉ፡፡(2) "አብርሆት ቤተ-መጻሕፍትን የሚሰራ መንግስት እንዴት ነው በመጻሕፍት ላይ ተጨማሪ እሴት ታክስ የሚጥለው?'' የሚሉት አቶ ወንድሙ "ይሄ ወደ ፊት እየሄዱ ወደ ኋላ መመለስ ነው'' በማለት ውሳኔውን ይሞግታሉ፡፡


photo source: The Reporter Ethiopia

አቶ ወንድሙ ኢብሳ

ከዚህ ቀደም በ1994 ዓ.ም የወጣው የተጨማሪ እሴት ታክስ አዋጅ ወደ አገር የሚገቡና በአገር ውስጥ የሚሸጡ መጻሕፍት እና የታተሙ ጽሑፎች የሚኒስትሮች ምክር ቤት በሚያወጣው ደንብ መሠረት ከታክስ ነፃ የሚያደርግ ነበር፡፡ አዲሱ አዋጅ ግን ለሀያ ዓመታት በስራ ላይ የቆየውን ይህንን አዋጅ የሚሽር ነው፡፡




photo source: Facebook | Melese Book Store

“የመጻሕፍ ህትመት ስራ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተቀዛቀዘ ነው” ይህንን ሀሳብ የሚሰጡት በእታፍዘር ማተሚያ ቤት የሚሰሩት አቶ አብርሃም አሰፋ ናቸው።

ለመጻሕፍት ህትመት ዘርፍ መዳከም “የአሳታሚ ድርጅት አለመኖር፤ የማንበብ ባህል ደካማ መሆን፤ እና የሚታተሙ መጻሕፍት ኮፒ ዝቅተኛ መሆንን” አቶ አብርሃም በምክንያትነት ያስቀምጣሉ።


በቅርብ አመታትም ቢሆን አዳዲስ መጻሕፍት ከ ሶስት ሺህ ወይ አምስት ሺህ በላይ እንደማይታተሙ የሚገልጹት አቶ አብርሃም በአሁኑ ወቅት የህትመት ዋጋም ከፍ በማለቱ የሚታተሙ መጻሕፍት ቅጂአቸው እየወረደ መምጣቱን ይናገራሉ።

በአሁኑ ወቅት ለመጀመሪያ ጊዜ የሚታተም አዲስ መጽሐፍ “ብዙ” ከተባለ እስከ 3 ሺ ቅጂ ቢታተም ነው። የመጽሐፍ ሕትመት ዋጋም በቀደሙት አመታት ከነበረው ከ 30 እስከ 40 በመቶ ጭማሪ እንደታየበት አቶ አብርሀም ያብራራሉ።

የማሳተም ፍላጎት ያላቸው ደራሲያን መጨመራቸውን የሚናገሩት አቶ አብርሃም አሳታሚ ድርጅት ባለመኖሩ የማሳተም አቅም ያላቸውም ፀሐፊዎች ውስን እየሆኑ ስለመምጣታቸውም ይገልጻሉ።

## የደራሲያን አበሳ እና የአሳታሚ ድርጅት አለመኖር

በቅርቡ ደማቆቹ የተሰኘውን 8ኛውን መጽሐፍ ለአንባቢያን ያደረሰው ደራሲ ሌሊሳ ግርማ የህትመት ዋጋ እየናረ መምጣቱን ይናገራል። ሌሊሳ በ2016 ዓ.ም. ሐምሌ ወር 2500 ቅጂ ለማሳተም ያወጣው ወደ 300ሺ ብር ገደማ ነው። ደራሲው የቀደመ መጻሕፉን በ2500 ቅጂ ለማሳተም ከ 2 አመት በፊት ያወጣው ወጪ ወደ 190ሺ ብር ገደማ እንደነበር ያስታውሳል።



የመጻሕፍቱን ዋጋ የሚተምነው ደራሲው ቢሆንም አሁን ባለው የህትመት ዋጋ ውድነት አዲስ መጽሐፍ በ400 ወይ 500 ብር ዋጋ ካልተተመነ የወጣበትን ወጪ ለማስመለስ አስቸጋሪ መሆኑን ሌሊሳ ይገልጻል::

ከዛ ባለፈ የመጻሕፍት ስርጭት ችግር መጽሐፍት የወጣባቸውን ወጪ ለማስመለስ እንኳን የማያስችል እንደሆነ የሚገልጸው ሌሊሳ “መጻህፍት አዟሪዎችም አያዋጣንም ብለው ከዘርፉ እየወጡ በመሆኑ” መጻሕፍትን ማግኘት የሚቻለው በመደብሮች ብቻ እየሆነ መምጣቱን ተናግሯል::

አንድ ደራሲ የህትመት ዋጋ በመናሩ ምክንያት የሚያሳትመው ትንሽ ቅጂዎችን ከሆነ የሚያሳትምበት ገንዘብ ከፍ ይላል። በተቃራኒው ከፍ ያለ ቅጂ የሚያሳትም ከሆነ ዝቅ እያለ ይሄዳል። ይሄ የሕትመት ያልተጻፈ ህግ ነው::
የህትመት ዋጋ መናር፤ አሳታሚ አለመኖሩ እንዲሁም የመጻሕፍት ስርጭት እና የክፍፍል ችግር የደራስያን የዘመናት አበሳ ሆኖ ቀጥሏል::

ከ4 አመታት በኃላ በቅርቡ አራተኛ እና አምስተኛ መጽሐፏን ለአንባቢያን ያደረሰችው ደራሲ ህይወት እምሻው የመጻሕፍት ስርጭት እና የክፍፍል ሂደት የዘመናት የደራሲያን ፈተና ሆኖ መቀጠሉን ትናገራለች:: ደራሲ ገንዘቡን አውጥቶ ካሳተመ በኋላ የሚሄድባቸው አከፋፋዮች ቁጥር ማነስ “የደራሲያንን የድርድር አቅም እየጎዳ” መሆኑን የገለጸችው ህይወት፤ በክፍፍል ሂደቱም “ለደራሲው የማይመቹ ብዙ ችግሮች አሉ” ስትልም ትገልጻለች::

የመጻሕፍት አዟሪዎችም ከጊዜ ወደ ጊዜ መጻሕፍትን ከማዞር ስራ እየወጡ ነው:: ምክንያቱም አዟሪዎች ከስራው ክብደት አንጻር የሚያገኙት ገንዘብ በቂ ባለመሆኑ እንደሆነ እንደሆነ ይነሳል::

መጻሕፍትን በተገቢው መንገድ ለአንባቢያን ለማቅረብ አዟሪዎችየሚጫወጡትሚናትልቅመሆኑንየምትናገረው ህይወት አዟሪዎች ከዘርፉ እየወጡ በመሆኑ ምክንያት መጻሕፍትን ለመግዛት አስቦበት መደብር የማይሄድ ሰው መጻሕፍትን ማግኘት የማይችልበት ሁኔታ እየተፈጠረ መሆኑን ታስረዳለች። የንግድ ሰንሰለቱም እየተበጠሰ ስለመሆኑም ትገልጻለች::

ይህ በእንዲህ እንዳለ ለዘመናት የደራስያን አበሳ ሆኖ የቀጠለው የደራሲያን አሳታሚ የማጣት ችግር ነው:: በአጼ ኃይለሥላሴ ዘመን አንድ ደራሲ ድርሰቱን የሚያስነብበው በራሱ ገንዘብ አሳትሞ፣ ራሱ አከፋፍሎ፣ የማከፋፈሉን ሥራ ሠርቶ ነበር::

ደራስያኑ የቤት ካርታ ለማተሚያ ቤቱ አስይዘው፣ ወይም ደሞዝተኛ የሆነ ዋስ ጠርተው፣ ወይም ከቤተመንግሥት ሹማምንት ጋር ተወዳጅተው ወደ ማተሚያ ቤት ዘልቀው መጽሐፎቻቸውን ያስነብቡ እንደነበር አያልነህ ሙላት፤ “ደራስያንን ለማፍራትና ለማበረታታት ምን መደረግ አለበት?” በሚል ርዕስ በ1985 ዓ.ም በሠሩት ጥናት ጠቁመዋል::(4)

በዘመነ ደርግ የአሳታሚነት ታሪክ የኢትዮጵያ መጻሕፍት ድርጅት እና ኩራዝ አሳታሚ ድርጅት የብዙ ደራሲያን ስራ ለህዝብ እንዲደርስ በህትመቱ ዘርፍ ከፍተኛ ሚና ተጫውተዋል። (5)

በኦክስፎርድ ዩኒቨርስቲ ድርጅት ባልደረባ በነበሩት አቶ ተስፋዬ ዳባ የተቋቋመው “የኢትዮጵያ መጻሕፍት ድርጅት” አሳታሚ በርካታ ቁጥር ያላቸውን የደራስያን ሥራዎች ተቀብሎ ለህትመት አብቅቷል::
ኩራዝ አሳታሚ ድርጅትም የሶሻሊዝም ርዕዮተ አለምን ከማስተዋወቅ ባለፈ በአሥር ሺህዎች በሚቆጠር ቅጂ እያሳተመ ድርጅቱ ራሱ በመላ ሀገሪቱ በከፈታቸው ከሰላሣ በላይ ቁጥር ባላቸው የመጻሕፍት መደብሮች የኅትመት ውጤቶቹን በማሰራጨት የንባብ ባህል መዳበር ያበረከተው አስተዋፅኦ ላቅ ያለ ነው::

የኢሕአዴግ መንግስት ሲመጣ የኢትዮጵያ መጻህፍት ድርጅት ከገበያው ሲወጣ ኩራዝ አሳታሚ ድርጅትም ወደሜጋ አሳታሚነት ተቀየረ:: ሜጋ አሳታሚ ለጥቂት ዓመታት የነባርና የአዳዲስ ደራስያን ሥራዎችን ሲያሳትምና ሲያከፋፍል ቆይቶ በትምሕርት መርጃ መጻሕፍት፣ በሕጻናት፣ በሙያዊ መጻሕፍትና በመሳሰሉት ላይ ብቻ ትኩረቱን አሳረፈ::

የአሳታሚ መኖር በረከቱ የተትረፈረፈ እንደሆነ ደራሲ እንዳለ ጌታ ከበደ (ዶ/ር) ይገልጻል። (6) ለደራሲው



እንዳለጌታ ከበደ(ዶ/ር)

photo source: Endalegeta Facebook page

እንቅፋት ከሆኑበት ፈተናዎች መካከል ዋነኛው አሳታሚ ማግኘት ወይም ማሳተሚያ ገንዘብ ፈልጎ ማግኘት ነው:: በዚህ ረገድ በአሁኑ ወቅት አንድ ደራሲ ተበድሮ መከራ አይቶ ካሳተመ በኋላ መጻሕፍት አከፋፋዮች መጽሐፉን ለማከፋፈል ከዋጋው ላይ 35 እስከ 40 በመቶ ክፍያ እንደሚቀበሉ የደራሲያን ማህበር ፕሬዝዳንት አቶ አበረ ይናገራሉ::



photo source: Al ain News

ደራሲ አበረ አዳሙ

ለምሳሌ አንድ ደራሲ አንዱን መጻሕፍ በ400 ብር ዋጋ እንዲሸጥ ዋጋ ካወጣለት፤ ከዋጋው ላይ 40 በመቶውን የሚወስደው አከፋፋዩ ነው:: በዚህ ስሌት መሰረት ከአንዱ መጽሐፍ ላይ አከፋፋዩ 140 ብር የሚወስድ ሲሆን ደራሲው 260 ብር የሚወስድ ይሆናል::

ይህ ማለት መጽሐፍት አከፋፋዮች ድርሻቸውን የሚያሰሉት ከትርፍ ላይ ሳይሆን ከአጠቃላይ የመጽሐፉ ሽያጭ ላይ ነው:: በዚህ ስሌት ደራሲው 260 ብር ቀሪ ቢኖረውም ለማሳተሚያ እስከ 200 ብር ሊያወጣ ይችላል:: ታዲያ ደራሲው የሚገኘው ትርፍ በወፍ በረር ስሌት ከ60 እና 70 አይበልጥም ማለት ነው:: ይህ ደግሞ የመጽሐፍ ምረቃ፤ የማስታወቂያ የሚሉትን ወጪዎች ታሳቢ ሳያደርግ ነው::

በዚህም ለደራሲው የሚደርሰው ገንዘብ ልፋቱን ያገናዘበ እንደማይሆን የሚገልፁት አቶ አበረ "የደራሲ መከራ ብዙ ነው" ሲሉ ይገልጻሉ:: ከዛ በተጨማሪ የተወሰኑ አከፋፋዮች ብቻ መጻሕፍትን በካሽ ገንዘብ ገዝተው ለደራሲ እንደሚያከፋፍሉ የገለጹት አበረ ነገር ግን አንዳንድ አከፋፋዮች ደራሲያን ገንዘባቸውን ለመቀበል በማመላለስ ደራሲያንን ማማረራቸው የተለመደ መሆኑን ያነሳሉ::

## የንባብ ባህል መዳከም እና የዲጂታል አማራጮች

በኢትዮጵያ የኤሌክትሮኒክ ሚዲያ መዘመን ምክንያት የህትመት ሚዲያው ለአደጋ በመጋለጡ የንባብ ልምድ መዳከሙን የደራሲያን ማህበር ፕሬዝዳንት አቶ አበረ አዳሙ ይገልጻሉ::

የንባብ ልምድ አለመዳበር መሰረታዊ ችግር መሆኑን የሚገልፁት አቶ አበረ በዚህ ችግር ላይ የኤሌክትሮኒክ ሚዲያ መዘመን "ብዙ ሰው ከመጽሐፍ ይልቅ ስልኩን ይዞ እንዲገኝ ምክንያት ሆኗል" ይላሉ:: በዚህ ምክንያትም በደርግ ዘመን፣ በቀዳማዊ ሀይለስላሴ ዘመን ከነበረው አንባቢ ይልቅ አሁን እጅግ በጣም የቀነሰ መሆኑንም ይናገራሉ::

ማህበረሰቡ ቀልቡ የተያዘው በስልኩ በሚያገኛቸው ዲጂታል አማራጮች እንደሆነ ደራሲ ህይወት እምሻው ትናገራለች:: "የኢትዮጵያ ህዝብ አያነብም በሚለው ነገር አልስማማም" የምትለው ህይወት ዲጂታል አማራጮች በመጠቀም ተደራሽ መሆን እንደሚያስፈልግ ነው የምትሞግተው::

ይህንን እድልም በመጠቀምም መጻሕፍቶቿንም በትረካ እና በኢ-ቡክ እያደረሰች ነው:: መጻሕፍትን በዲጂታል አማራጭ ለማቅረብ ያለው ተሳትፎ "አመርቂ እንዳልሆነ" የምትገልፀው ህይወት ደራሲያንም ስራዎቻቸውን በዚህ መልኩ ለማቅረብ ፈቃደኛ እንዳልሆኑ ሆኖም ጊዜው እየተለወጠ በመሆኑ ከጊዜው ጋር መሄድ አስፈላጊ መሆኑን ትገልጻለች::

መጻሕፍትን ተርኮ በማቅረብ የሚታወቀው "ተራኪ" የተሰኘው ኦዲዮ ቡክ እና ፖድካስት ከ150 በላይ መጻሕፍትን በመተረክ በተራኪ መተግበሪያ ላይ እንዳቀረበ የድርጅቱ ዋና ስራ አስፈፃሚ ናሆም ፀጋዬ ይናገራል::

መጻሕፍቱ ተተርከው ለገበያ የቀረቡት ከ80 እስከ 150 ብር በሚደርስ ዋጋ ነው:: ለአድማጮች መጻሕፍቱን ለመተረክ ደራሲያን ወጪ እንደማያወጡ እና ሁሉም የፕሮዳክሽን ስራ በድርጅቱ እንደሚከወን ናሆም ይናገራል::

ከደራሲያን ጋር ውል ተፈራርሞ የሚሰራው ይህ ስራ በአማካይ ከ45 እስከ 50 በመቶ ደራሲያንን ከስራዎቻቸው ተጠቃሚ የሚያደርግ እንደሆነ አቶ ናሆም ይገልጻል፡፡



photo source: Teraki App

ደራሲያን ስራዎቻቸውን ለአድማጮች በትረካ መልክ ለማቅረብ ፍላጎት እንደሌላቸው ይነገራል፡፡ ለዚህ ምክንያቱ "ነገሩን ካለመረዳት ነው" ያላል ናሆም፡፡

ይህም ለዘርፉ ፈተና እንደሆነ የሚገልጸው ናሆም መጻሕፍትን በነጻ ማዳመጥ ለለመደ ማህበረሰብ በክፍያ ማስለመድ አስቸጋሪ መሆኑንም አልደበቀም፡፡

ተራኪ ስራውን ከጀመረ ከሶስት አመት በላይ ሆኖታል፡፡ በነዚህ አመታት መጻሕፍትን በትረካ ማቅረብ በአጠቃላይ ከአመት አመት እየተሻሻለ፤ ፍላጎቱም እየጨመረ መሆኑን ናሆም ያስረዳል፡፡

ይህ የዲጂታል አማራጭ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተለመደ መምጣቱ እንደማይቀር የሚናገረው ናሆም ከባለፈው አመት ጥር ወር ጀምሮ ባለው ጊዜ በተራኪ መተግበሪያ ላይ ፖድካስትን ጨምሮ የኦዲዮ ቡክን የሚያዳምጡ 234ሺ ተጠቃሚዎችን እንዳፈራ ገልጿል፡፡

ይህ አሃዝ ከቀደመው አመት ጋር ሲነጻጸር በእጥፍ መጨመሩን የሚናገረው ናሆም በቀደመው አመት የነበረው የተጠቃሚዎች ቁጥር 104ሺ እንደነበር ጠቅሷል፡፡

## ዘርፉ የተረጋጋ እንዲሆን ምን ምክረ ሀሳብ ቀረበ?

የህትመት ዋጋ መናርን ለመከላከል ወረቀት በሀገር ውስጥ እንዲመረት ጥረት መደረግ እንዳለበት የደራሲያን ማህበር ፕሬዝዳንት አበረ አዳሙ ሀሳብ ይሰጣሉ፡፡ መንግስትም ባለሀብቶች በወረቀት ማምረት ዘርፍ እንዲሰማሩ ማበረታታ ማድረግ አስፈላጊ መሆኑንም ይጠቅሳሉ፡፡ "ወረቀትም ቢቻል በመንግስት በኩል ወደ አገር ውስጥ እየገባ ለትክክለኛ አታሚዎች በተመጣጣኝ ዋጋ የሚከፋፈልበት መንገድ ቢመቻች" የሚል ሀሳብም ያቀርባሉ፡፡

"ከመጻሕፍት ውጪ፤ ከእውቀት ውጪ አገርን ለማልማት ደፋ ቀና ማለት የሚታሰብ አይደለም" የሚሉት አቶ አበረ፤ የወጣቱ አእምሮ በንባብ መገንባት እንዳለበት እምነት አላቸው፡፡ "መጻሕፍት እንዲኖሩ፣ በብዛት እንዲታተሙ፣ እንዲሰራጩ ከቀረጥ ነፃ መሆን አለባቸው" ሲሉም አጽእኖት ይሰጣሉ፡፡

ጠንካራ አሳታሚ ድርጅት ቢኖር ለዘርፉ ጠቃሚ እንደሚሆን አቶ አይናለም ይመክራሉ፡፡ የደራሲ ሚና መጻፍ ብቻ መሆን እንሚገባው የሚገልጹት አቶ አይናለም አሳታሚ ድርጅቶች ቢኖሩ ደራሲ መጽሐፍ ጽፎ የአርትኦት፣ የማተም እና የሽያጭ ጣጣ ውስጥ በመግባት አይቸገርም ባይ ናቸው፡፡ በዚህ ሂደት ደራሲው ስራውን ለአሳታሚ ድርጅት በማስረከብ የሮያሊቲ ክፍያ ተከፍሎት ወደ ቀጣይ ስራ መሄድ የሚያስችለው መሆኑን ያብራራሉ፡፡

በኢትዮጵያ ድርጅቶች፣ ባንኮች፣ የቴሌኮም ኩባንያዎች ለመዘቀኞች እና ሌሎች የጥበብ ድጋፍ ያደርጋሉ፡፡ ይሁን እንጂ እነዚህ አካላት እንደሌላው የጥበብ ዘርፍ ለስነጽሑፍ ሰዎች እና ስራዎች ድጋፍ እንደማያደርጉ ህይወት እምሻው ታነሳለች፡፡

ስነጽሑፍ እንደ ጥበብ ስራ ተቆጥሮ፤ አስፈላጊ እንደሆነ ታምኖበት በድርጅቶች መደገፍና መበረታታት እንዳለበት የምትመክረው ህይወት ቢያንስ አቅም ለሌላቸው እና ማሳተም ለማይችሉ ደራሲያን ድጋፍ መደረግ እንዳለበትም ነው ምክረ ሐሳብ ያቀረበችው ፡፡

## አሁናዊ የመጻሕፍት ዋጋ እና የገበያ ሁኔታ

5 መደብሮችን መሰረት አድርጎ በተሰራው መጠነኛ የዋጋ ጥናት፦

### የመጽሐፍ ዋጋ ከቀደመው አመታት ጋር ሲነፃፀር

- ሁለቱ መደብሮች ዋጋው በከፍተኛ ሁኔታ እንደጨመረ፤
- ሁለቱ ደግሞ በመጠኑ መጨመሩን፤ አንድ መደብር ደግሞ መቀነሱን ገልጸዋል።

### በ5 መደብሮች በተሰበሰበ መረጃ

- አዲስ የሚታተም አንድ መጽሐፍ የሚሸጥበት ከፍተኛ ዋጋ በአማካይ 962 ብር ከ5 ሳንቲም ነው።
- በተመሳሳይ አዲስ የሚታተም አንድ መጻሕፍ የሚሸጥበት ዝቅተኛ ዋጋው በአማካይ 202 ብር ነው።
- በአሁናዊ ገበያ አዲስ የሚወጣ አንድ መጻሕፍ ከጀርባ የሚለጠፈው ከፍተኛ ዋጋው በአማካይ 1100 ብር ነው። (3)
- በተመሳሳይ አዲስ የሚወጣ አንድ መጻሕፍ ከጀርባ የሚለጠፈው ዝቅተኛ ዋጋው 242.5 ብር ነው።

### በመደብሮቹ በብዛት የሚስተናገዱት መጽሐፍ ሸማቾች

- 4 መደብሮች ወጣቶችን
- 2 መደብሮች ጎልማሶችን መርጠዋል።

### በብዛት ገዢ ያላቸው የትኞቹ የመጽሐፍት አይነቶች እንደሆኑ ለቀረበ አማራጭ

- የልቦለድ መጻሕፍት በ4 መደብሮች ላይ በብዛት ገዢ አላቸው።
- ሳይኮሎጂ በተመሳሳይ በ4 መደብሮች
- ታሪክ በ 3 መደብሮች
- ትርጉም በ 2 መደብሮች በብዛት ገዢ አላቸው ።

## የግርጌ ማስታወሻ


1) (ቃላት ኪናዊ መፅሄት ቅፅ 12 ነሐሴ 4, 2016 ዓ/ም)
2) የኢትዮጵያ ደራሲያን ማህበር በመፅሐፍት ላይ ተጨማሪ እሴት ታክስ መጨመሩን ተከትሎ ነሀሴ 8 2016 ባደረገው ውይይት ላይ የናገሩት
3) በብዙ መደብሮች መጻሕፍት የሚሸጠው ጀርባቸው ላይ ባለው ዋጋ አይደለም። መደብሮች እንደ መጻሕፍቱ አይነት ከ20-50 በመቶ ቅናሽ አድርገው እንደሚሸጡ ይገልጻሉ።
4) አቶ አያልነህ ሙላት ይህን ጥናት ያቀረቡት፣ ግንቦት 1985 ዓ.ም ተዘጋጅቶ በነበረው ለነፃ መጻሕፍት ገበያ ኮንፈረንስ ነበር።
5) የኢትዮጵያ የህትመት ኢንዱስትሪ ችግሮች፣ ስጋቶችና መፍትሄዎች ጥናት። አስጠኚ፤ የኢትዮጵያ አሳታሚዎችና አታሚዎች ማኅበር፤ ጌታቸው በለጠ መስከረም 2008 ዓ.ም (ያልታተመ)
6) የአንድ ኢትዮጵያዊ ደራሲ ሕማም (ከትናንት እስከ ዛሬ) እንዳለጌታ ከበደ (ዶ/ር) ሚያዚያ 8 /2010ዓ.ም



### ስለ አዘጋጁ

የዚህ ጹሑፍ አዘጋጅ አልታየህ ኪዳኔ ከአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ በጋዜጠኛነት የተመረቀ ሲሆን በአሁን ሰዓት በጋዜጠኛነት ሞያ እያገለገለ ይገኛል።

+251 932 47 9632 altayehkidane@gmail.com




# ተፈጸመ!

## ግጥም

ከ ዙፋን ክፍሌ

# ተፈጸመ!

## ዙፋን ክፍሌ

መደበቅ ብርጭቆ ጀርባ?
መንጎድ በጢስ አንቀልባ?
የለም!
እንደሱ አይደለም!
መጋፈጥ ነው ከእውነታው
መታረቅ ነው ከሁኔታው
ቀድሞ አቤት ሕመሙ፥ኋላ አቤት ውለታው!

ወልይ አዋቂ ማማከር፤
ለ ኮከብ ለዕጣ ለገድ?
ለቆሪጥ ላድባር መገበር፤
ለሼህ ለአቡን ማሸርገድ?
ስድሳ አራት መቁጠሪያ መቁጠር፤
አርባ አንድ ፥ አርባ አንድ  መስገድ?
አርባ አንዴ ኪራላይሶን?
እኮ - ጸሎት ፈውሶን?
እኮ - ምፅዋት ሊረባን?
እንጀ ሊበልጠው እንባን?

የለም!
እንደሱ አይደለም!

የኀውሸት ጠበል አትጠመቅ፣
ዲያብሎስን ለማሳጣት፤
ከገዛ ራስ ነው መታረቅ፣
ከራስ ነው አርነት መውጣት!

አያሽልም፣ጸሎት ዱዓ - የሼህ ያኀቡን
የባለዛር፣ የቃልቻ - ጫትና ቡን
የለም!
እንደሱ አይደለም!

ጅራፍ ብላ ጠጣ ጨንገር
ሲናገሩህ አትናገር
አምላክ ነህ ሰው?
ለሰው..፤
ግራ ይግባው ይደናገር!

አትመልስለት ሲጠራህ
ቆይ ጥቂት ጲላጦስ ይፍራህ..፤

ቆይማ አጉል ይስደቡህ
ራስ ራስህን ይደብድቡህ..፤
እ? ሰደቡህ?
ደበደቡህ?
ቀጠቀጡህ በሸንበቆ?
አጥንት ቀረህ ሥጋህ አልቆ?

ምን ቀረህ ከኀንግዴህ ወዲያ..?
ካሳለፍህ የጭንቀት ጽዋ፥ከጠገብህ የስቃይ እራት
ተቀብተሃል የደም ቅብ፥ነግሠሃል ባማረ ስራት
ቀራኒዮ አንባ ውጣና፥ተፈጸመ በል በኩራት!

ተፈጸመ!






# ወጣት ዲፕሎማቶች ለምን የሉንም ?

ኢትዮጵያ በዓለም - አቀፍ መድረኮች የሚወክሏትን ወጣት ዲፕሎማቶች ለምን አጣች? አልፎ አልፎስ የምናያቸው ወጣቶች ቶሎ ከእይታችን የሚጠፉበት ምክንያት ምንድነው?

ደምሠው ሺፈራው

የዚህ ጹሑፍ መነሻ ሐሳብ፥ ኢትዮጵያ ባላት የወጣቶች ቁጥር በዓለም አቀፍ ደረጃ ከቀዳሚዎቹ ተርታ የምትመደብ ሀገር ሆና ሳለ ነገር ግን ወጣቶቿ በፖለቲካዊ፣ በምጣኔ ሃብታዊ እና ሌሎች ወሳኝ የሆኑ ጉዳዮች ላይ ያላቸው ተሳትፎ እጅግ ዝቅተኛ ነው ተብሎ ስለሚወቀስ፤ አልፎም የዲፕሎማሲው ሥራ ለወጣቶች ያልተፈቀደ በሚመስል መልኩ የመሳል አዝማሚያ ስለሚስተዋል ምን ይሆን ምክንያቱ? ምንስ መደረግ አለበት? ሲል የሚመለከታቸውን አካላት ቃለመጠይቅ በማድረግ ‹‹ለምን ?›› የሚል ጥያቄ በአንባቢያን ዘንድ ለመፍጠር የተዘጋጀ ነው:::

የዲፕሎማሲው ዘርፍ በተለይ ባለፉት ጥቂት ዓመታት ውስጥ በኢትዮጵያ በጉልህ እየታዩ ባሉ ፈተናዎች ውስጥ በብዙ የተፈተነችበት ስለመሆኑ ብዙ ማሳያዎች ማቅረብ ይቻላል፡፡ ዲፕሎማሲያችን ምን ያክል ውጤታማ ነው የሚለውን ምዘና ለጊዜው ብናቆየው እንኳን ዘመኑን የዋጀ እና ዘመኑን የመሠሉ በሳል ወጣት ዲፕሎማቶች ወደፊት ቀርበው አለመታየታቸው ግን የአደባባይ ሀቅ ነው፡፡ ለዚህም የዲፕሎማሲ ፖሊሲያችን በሰፊው ትችት ይቀርብበታል፡፡

አልፎ አልፎ በዚህ ዘርፍ አሉ ተብለው የምናያቸው ወጣቶች ስያሜውን ከፊት የመለጠፍ አባዜ እንጂ በብቁ የሰለጠኑና ቦታው የሚመጥነውን ክህሎት ያሟሉ ሆነው አይታዩም:: አልፎ አልፎ የምናያቸው ብቁ ወጣቶች ደግሞ በዚሁ መስመር ሲቀጥሉ አይስተዋልም::

አሁን ላይ በበይነ መረብ እና በሌሎች አማረጮች የዲፕሎማሲ እንቅስቃሴ ለመስራት ጥረት ከሚያደርጉ ወጣቶች መካከል ያነጋገርናት ወጣት ሳምራዊት ክፍሉ "ወጣቶች በዲፕሎማሲው ዘርፍ የመስራት አቅም እና ብቃቱ እንደሌላቸው መታሰቡ እንዲሁም በዘርፉ በዕድሜ መብሰል ከሌሎቹ መስፈርቶች በተለየ መልኩ ትኩረት የሚሰጠው መሆኑ ወጣቶች ወደፊት እንዳይመጡ አድርጓል ብዬ አምናለሁ" ትላለች::

"በዚህም ምክንያት ወጣቱ ጋር ያለውን አቅም በውጪ ግንኙነት እና ዲፕሎማሲው በኩል መጠቀም እንዳንችል አድርጎናል፤ በተለይም መንግስት ከሰልጠና ጀምሮ ለወጠቶች እድሉን ከመፍጠር አኳያ ብዙ የሚጠበቅበት ቢሆንም በተግባር ግን እምብዛም አይስተዋልም" ትላለች::

ፖለቲከኛው አቶ ጌትነት ወርቁ የሄው ጉዳይ አብዝቶ እንደሚያሳስባቸው ነግረውናል:: "በሀገራችን ውስጥ የሚገኙ ኤምባሲዎች እንዲሁም የተለያዩ አለማቀፍ ተቋማት ውስጥ በርካታ ወጣቶችን ማየት የተለመደ ነገር ቢሆንም በኢትዮጵያ ኤምባሲዎች እንዲሁም በምትወከልባቸው ዓለማቀፍ እና አህጉር አቀፍ ተቋማት ውስጥ ግን ኢትዮጵያዊ ወጣት ማየት ከባድ ነው" በተጨማሪም "ባለፉት ጥቂት አመታት በተለያየ ጉዳዮች ላይ ያጋጠሙንን አለማቀፍ ጫናዎች በመደበኛው የዲፕሎማሲ አቅም መወጣት ሳይቻል በቀረበት ጊዜ በግል ተነሳሽነት በዲፕሎማሲ ስራ ላይ ሲንቀሳቀሱ የነበሩ ጥቂት ወጣቶች ያመጡትን ውጤት ማስታወስ በቂ ነው" ሲሉም ማስረጃ ይጠቅሳሉ::

"ነገር ግን" ይላሉ አቶ ጌትነት "እነዚህን ወጣቶች ይበልጥ እንዲበረቱ ብሎም ሌሎች ወጣቶችን እንዲያሠለጥኑ እንዲሁም በዲፕሎማሲው በኩል ከመንግስት ጋር ተቀራርበው እንዲሰሩ ከማድረግ ይልቅ ነገሮች የረገቡ ሲመስሉ ከነመፈጠራቸውም ሲረሱ ይታያል:: ይህም በቀጣይ ሌሎች ወጣቶች ወደፊት እንዳይመጡ የማድረግ እድሉ ሰፊ እንደሆነ መገንዘብ ያስፈልጋል" በማለት በተለይም መንግስት ትኩረት ሊሠጠው የሚገባው ጉዳይ እንደሆነ ማሳሰቢያ አዘል የሆነ መልዕክታቸውን አስተላልፈዋል::

በተባበሩት መንግስታት ድርጅት አማካሪ እና የምጣኔ ሀብት ባለሙያው ዶ/ር ቆስጠንጢኖስ በረኸተስፋ በበኩላቸው "ዓለማቀፍ ጫናዎች በሚፈጠሩበት ጊዜ መንግስት በራሱ ከሚያደርጋቸው የማሳመን እንቅስቃሴዎች በላቀ መልኩ በቂ እውቀት እና ችሎታው ያላቸው ወጣቶች የሚፈጥሩት ንቅናቄ የተሻለ ተቀባይነት እንዳለው የሌሎች አገራት ተሞክሮ ያሳያል" ይላሉ::

"ነገር ግን በመንግስት በኩል በተለይም በዲፕሎማሲው ዘርፍ ከወጣቱ ጋር ተቀራርቦ መስራት እና ዕድሉን በማመቻቸት በኩል ፍላጎት አለመኖር እና ልምድም የሌለን መሆኑ ጠንካራ ዲፕሎማሲያዊ አቅም እንዳይኖረን ካደረጉ ምክንያቶች መካከል በግንባር ቀደምነት የሚነሳ ነው" ብለዋል::

> በሀገራችን ዲፕሎማቶችን ከታች ከትምህርት ቤቶች ጀምሮ የማብቃት እና መንገዱን እንዲያውቁት የማድረግ ልምድ የለም፤ ይህም በዲፕሎማሲው ዘርፍ እንደ አገር ይበልጥ ደካማ እየሆንን እንድንሄድ እያደረገን ይገኛል።
>
> አቶ ጌትነት ወርቁ




photo source: Getinet Worku Fb page

በተለይም ደግሞ ጉዳዩ በቀጥታ የሚመለከተው የውጪ ጉዳይ ሚንስቴር ፍላጎቱ ያላቸውን ወጣቶች መለየት፤ ተጨማሪ ስልጠናዎችን ማመቻቸት እና በዲፕሎማሲው ዘርፍ ላይ ለውጥ ማምጣት የሚችሉ ወጣቶችን ዕድል መስጠት አለበት ነው ያሉት።

በኢትዮጵያዊ በዲፕሎማሲው ዘርፍ ወርቃማው ጊዜ ነው በሚባልበት 1950ዎቹ ላይ የውጪ ጉዳይ ሚንስትር በመሆን ያገለገሉት ከተማ ይፍሩ ስማቸው የገነነ ዲፕሎማት ነበሩ፤ ለአፍሪካ ህብረት ምስረታም የነበራቸው አስተዋፆ አሁንም ድረስ የሚታወስ ሲሆን በወቅቱ በንጉሱ ተሹመው ከነበሩት ሚንስትሮች መካከል እርሳቸው ወጣት እንደነበሩ ይነገራል።

አቶ ሙሉጌታ ከተማ የቀድሞው የውጪ ጉዳይ ሚንስትር ከተማ ይፍሩ ልጅ ናቸው፤ የዓለማቀፍ ግንኙነት አማካሪ የሆኑት አቶ ሙሉጌታ ከተማ ይፍሩም ከላይ የተነሱ ሀሳቦችን በመደገፍ ወጣቶችን በዲፕሎማሲው ዘርፍ በብዛት እና በጥራትም ጭምር መፍጠር ቢቻል አሁን ዓለም እየተጓዘ ካለበት ፍጥነት እኩል መራመድ እንድንችል አስተዋጾው የጎላ ነው ይላሉ።


photo source: Nahoo TV

አቶ ሙሉጌታ ከተማ

በተለይም ደግሞ ትልልቅ የሚባሉት ዓለማቀፍ ተቋማት አሰራራቸው የተወሳሰበ እና ቢሮክራሲው የሚበዛ እንደሆነ አንስተው ይህንን ውስብስብ አሰራር ተረድቶ በፍጥነት መንገድ አበጅቶ ከመስራት አኳያ የወጣቶች አስፈላጊነት በቀላሉ የሚታይ መሆን እንደሌለበት ያስረዳሉ።
ለዚህም "በዲፕሎማሲው ዘርፍ ብቁ ወጣቶችን ከማፍራት አኳያ በተለያዩ አለማቀፍ ድርጅቶች ውስጥ የተግባር ልምምዶችን ማመቻቸት እና ፍላጎቱ እና አቅሙ ያለቸውን ወጣቶች ደግሞ በመለየት ለሀገር መጥቀም እንዲችሉ እድሉን መንግስት ሊፈጥር ይገባል" ሲሉ መክረዋል።

"ቀደም ባሉት ሥርአቶች ወጣቶች እንደ ተባበሩት መንግስታት ባሉ ዓለማቀፍ ተቋማት ሄደው የተግባር ልምምድ እንዲያደርጉ ይደረግ ነበረ" በማለት "አሁን ደግሞ አዲስ አበባ የአፍሪካ ህብረትን ጨምሮ የተለያዩ አለማቀፍ እና አህጉራዊ ድርጅቶች መቀመጫ እንደመሆኗ መጠን በእጃችን ያለውን እድል በአግባቡ ልንጠቀምበት ይገባል" ሲሉ አሳስበዋል።
በተባበሩት መንግስታት ድርጅት የቀድሞ ምክትል ዋና ጸሀፊ የነበሩት ተገኘወርቅ ጌጡን(ዶ/ር) ስለዚሁ ጉዳይ አነጋግረናቸዋል።
እርሳቸውም በዲፕሎማሲው ዘርፍ ከፍተኛ ግነት የሚሰጣቸው ሀገራት ውስጥ ወጣቶች ለዘርፉ ፍላጎት እንዲኖራቸው እንዲሁም አለማቀፍ ተቋማት እንዴት ነው የሚሰሩት የሚለውን የሚያስተምሩባቸው ማዕከላትን አቋቁመው እንደሚሰሩ ገልጸው፤ «በእኛ ሀገር ግን በራሳቸው ጥረት የሚመጡት እንኳን እድሉን ሲያገኙ አይስተዋልም» ይላሉ።

> "የዓለማቀፍ ተቋማትን እና አጠቃላይ የውጪ ግንኙነት ሥራዎችን ለወጣቶች ክፍት ማድረግ እና በተግባር እየተማሩ እንዲመጡ ማድረግ ያስፈልጋል፣ በተለይም ደግሞ የውጪ ጉዳይ ሚንስቴር በኤምባሲዎች ውስጥ ወጣቶች እየሄዱ የተግባር ልምምድ እንዲያደርጉ የማመቻቸት ስልጣኑ አለው" ሲሉ ጠቁመዋል።

በጨማሪም መንግስትም ሆነ የሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች ዘርፉ ለአገር የሚኖረውን ጠቀሜታ ታሳቢ ባደረገ መልኩ ወጣቶችን ማብቃት እና ዕድሎች እንዲመቻችላቸው ማድረግ ላይ ትኩረት ሊሰጡት እንደሚገባ ተናግረዋል።

ኢትዮጵያውያን ወጣት ዲፕሎማቶችን እና መሪዎችን ማብቃት ላይ ትኩረቱን አድርጎ የሚሰራው «ሴፍ ላይት» የተሰኘ ተቋም በማቋቋም የበኩላቸውን ጥረት እያደረጉ መሆኑን የሚናገሩት የተቋሙ ሥልጠና እና ልማት ሀላፊ አቶ ስምኦን ጌትነት ናቸው።

ተቋሙ ከተመሰረተ ከ3 ዓመት በላይ የሆነው ሲሆን በእነዚህ አመታትም በተለይም በዲፕሎማሲው ዘርፍ ላይ ፍላጎቱ ያላቸውን ወጣቶች በመሰብሰብ ከፍተኛ ልምድ ካላቸው ዲፕሎማቶች እና አምባሳደሮች ጋር እንዲገናኙ እና ልምዳቸው እንዲካፈሉ ከማድረግ በተጨማሪም አቅማቸውን ሊያሳድጉ የሚችሉ ተከታታይ ሥልጠናዎችን እየሰጡ እንደሚገኙ ይናገራሉ።

ጉዳዩ የሀገር ጉዳይ እንደመሆኑ መጠን ከሚመለከታቸው መንግስታዊ ተቋማት ጋር ለመስራት ጥረቶችን ቢያደርጉም በተለይ ቀጥተኛ ባለድርሻ ከሆነው የውጪ ጉዳይ ሚንስቴር በኩል በቂ ትኩረት አለማግኘታቸውን ያስረዳሉ።

በአገራችን ወጣቶችን በአመራርነት እንዲሁም አገርን ወክሎ በሚደረጉ የዲፕሎማሲ እንቅስቃሴዎች ላይ እምብዛም ተሳታፊ እንዳልሆኑ የሚታወቅ ሲሆን በዚህ ዜሪያም ለውጥ ለማምጣት እንዲሁም ብቁ እና በአገራቸው ጉዳይ ላይ ውሳኔ የመስጠት አቅም ያላቸው ወጣት አመራሮችን ለመፍጠር የሚያስችሉ ተከታታይ የሥልጠና መድረኮችን በሴቶች እና ማኅበራዊ ጉዳዮች ሚንስቴር አማካኝነት እየተዘጋጀ እንደሚገኝ የሴቶች እና ማኅበራዊ ጉዳዮች ሚኒስትር ኤርጎጌ ተስፋዬ (ዶ/ር) ጥቅምት 9፣ 2016 ዓ/ም. በተካሄደ አንድ የወጣት መሪዎች ዙሪያ ባተኮረ መድክ ላይ ባደረጉት ንግግር ገልጸዋል።



photo source: MoWSA

ኤርጎጌ ተስፋዬ (ዶ/ር)

በተጨማሪም ወጣት አመራሮችን እና ዲፕሎማቶችን ማብቃት ላይ ትኩረት ሰጥተው የሚሰሩ ተቋማትን በልዩ ሁኔታ ድጋፍ እና እገዛ ለማድረግ ማቀዳቸውንም አስታውቀው ነበር። የዚህን አፈጻጸም በዚህ ጹሑፍ ማካተት ለጊዜው ባንችልም ግን የሚታይ ነገር፤ ለውጥ መፍጠር የሚችል ነገር ግን ወጣቱም ህዝቡም ይጠብቃል።

ኢትዮጵያ በዲፕሎማሲው ዘርፍ ወደ ኋላ እየቀረች እንድትሄድ ካደረጓት ምክንያቶች አንዱ እና ዋነኛው ፈጣን አስተሳሰብ እና አቅም ያላቸው ወጣቶች በዘርፉ ተገቢውን ቦታ ሊሰጣቸው አለመቻሉ ትልቁን ድርሻ የሚይዘው ጉዳይ ነው። ታዲያ ከከወጣቱም፤ መንግስትም እንዲሁም በዘርፉ ካሉ ልምድ ካካበቱ ዜጎች «ለምን ? » የሚል ቁጭት የሚፈጠረው መቼ ነው?

## ማጣቀሻ:

- ከተማ ይፍሩ የሰላም ዕድገትና የፓን አፍሪካኒዝም አቀንቃኝ፤ ሙሉጌታ ከተማ፤ 2015 ዓ/ም
- https://press.et/herald/?p=100205
- የሴቶች እና ማህበራዊ ጉዳዮች ሚንስትር ዶ/ር ኤርጎጌ ተስፋዬ ሀሳብ ጥቅምት 9 2016 በተካሄደው 3ኛው የወጣት መሪዎች ውድድር እና ጉባኤ መክፈቻ ላይ ካደረጉት ንግግር የተወሰደ ነው።
- ከላይ ከተጠቀሱት ማጣቀሻዎች ውጪ በጹሑፉ የተካተቱት ቃለ መጠይቆች ከዚህ ጸሑፍ አዘጋጅ ጋር የተደረጉ ናቸው።


### ስለ አዘጋጇ


የዚህ ጹሑፍ አዘጋጅ **ደምሠው ሺፈራው** ይባላል። ከአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ በስነ ልቦና ትምህርት የመጀመሪያ ዲግሪ አለው። በተጨማሪም አሁን ላይ በዚሁ ዩኒቨርስቲ የጋዜጠኝነት የመጨረሻ አመት የዲግሪ ተማሪ ነው።

+251 924 29 9242 Demssewshiferaw@gmail.com

# ስከ  ጤናችን

## የኩላሊት ጠጠር በሽታ

### የኩላሊት ጠጠር ምንድነው?



በሽንት ውስጥ ካሉ የተለያዩ ኬሚካሎች የሚመረቱ ናቸው። የማይንቀሳቀሱ እና በሽንት መልኩ የማይወጡ ከሆነ ሽንቱን ሊገድቡና ህመም ሊያስከትሉ ይችላሉ።

በተለይ ከካልሺየም የሚሰሩ ጠጠሮች (calcium oxalate) በብዛት የሚከሰቱት ናቸው።

### የኩላሊት ጠጠር ምልክቶች



ሆድ ህመም (የማያቋርጥ)



በአንድ ወይም ሁለት ጎን ላይ ያለ ከፍ ያለ ህመም



ትኩሳት



ቀለሙን የቀየረ ወይም ጠረን ያለው ሽንት ፣ ቶሎ ቶሎ መሽናት መፈለግ

⚠️ ህክምናው እንደ ጠጠሩ ዓይነት ሊለያይ ይችላል።

Concept Hub

©2024 | Addis Ababa,Ethiopia

www.concepthub.net